# ነፍሴ ወደ አምላኳ

Key of C

ተስፋዬ ጋቢሶ

C F C Dm7 G7
ነፍሴ ወደ አምላኳ ስጋም ወደ አፈሩ ሳይመ ለስ
C F C Em7 Dm7 G7
ቶሎ ቶሎ ብዬ ስራ ዬን ልጨርስ
C F C Dm7 G7
ነፍሴ ወደ አምላኳ ስጋም ወደ አፈሩ ሳይመ ለስ
C F C G7 C
ሌት ተቀን ልትጋና ስራዬን ልጨርስ።

Dm7 Bo7 Dm7 G
ሲተጉ የሚያገኛቸው ሲመጣ ጌታ ቸው
F G7 C Dm7
በመኪሊታቸው የሰሩ ምስጋና አላቸው
Dm7 Bo7 Dm7 G
አገልግሎቱን ያልናቀ በጥቂቱ ታምኖ
F C G7 C
ብድራቱን ይቀበላል ስራው ተፈት ኖ።
ነፍሴ ወደ አምላኳ . . .

አደራው ከቶ የማይገዳቸው ቸልተኞች
የጌታቸውን መመለስ የረሱ ዝንጉዎች
ዕድላቸው ለቅሶ ነውና ዋይታ እንዳይጠብቀኝ
መንፈስህ ዘወትር ያንቃኝ ለክብርህ አቁመኝ።
ነፍሴ ወደ አምላኳ . . .

ጥቂት ታይቶ በህዋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት
እንደሆን መቼ አጣሁት ከቶ የኔ ህይወት
እንግዲያውስ ታከተኝ ሳልል ልሩጥ ለጌታዬ
የሰነፍ ሰው ሞት እንዳልሞት ልትጋ በዓላማዬ።
ነፍሴ ወደ አምላኳ . . .

መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ አበቃሁኝ
ሃይማኖትን ጥብቄአለሁ ሩጫውን ጨረስኩኝ
እንደ ጳውሎስ ለማለት ተፈፀመ እንደ ኢየሱስ
ምስጋናዬንም እንዳቀርብ ለሰራዊት ንጉስ።
ነፍሴ ወደ አምላኳ . . .